# (ለማስታወስ ያህል)

# ፀረ ኢትዮያነት በአማራነት ካባ ሲውገረገር

# “ የአማራው ሕዝብ ከየት ወዴት” ላይ ሂሳዊ ትችት

**ታየ ቶላ ነሐሴ 1985**

1. *ማን ቢወልድ ማ?*

***የፅሁፉ ደራሲ ነኝ ያሉት አቶ አንጻርጋቸው ፅጌ ከ “ክልል 14” ምክር ቤት ቢወጡም ከኢሕዴን አባልነታቸው መልቀቃቸው አልተነገረም፡፡ ፅሁፋቸውም በይዘቱ ልንገራችሁ የሚለን ሀቅ ያው እጅ እጅ ሲለን የቆየው የህወሓት/ኢሕአዴግ ኢታሪካዊ ልፈፋን ከመሆኑ ባሻገር ደራሲው (ፅሁፋ ቸውን እንደልብ ወለድ ማንበቡ ይቀላልና) የውህደትና የመቀላቀል “ ችግር” ያስጨነቃቸው ስለ ሆኑ ማ ቢወልድ ማ ብለን በመጠየቅ ትችታችንን እንጀምራለን፡፡***

***ሀ / አቶ አንጻርጋቸው የኢሕዴን/ኢሕአዴግ አማኝ ተሚጋችና አባል ናቸው፡፡***
***ለ / አቶ አንጻርጋቸው በፃፉት ድርሰት (62 ገፅን-- ያውም በጥቅሶች ረዳት የተደረሰን--መፅሀፍ ማለቱ ማሾፍ ይሆናልና) አውቃለሁ በሚል ስለ ኢትዮጵያ ተማሪዎች እንቅስቃሴ ሆነ ስለ ኢሕአፓ ሆነ ስለ አማራው ሕዝብ የፃፉት ሁሉ አለማወቃቸውን የሚያስረግጥ ነው፡፡( ምናልባት ስለ ኖሩበት ለንደን ቢፅፉ ይሻል ነበር?)***
***ሐ / አቶ አንጻርጋቸው ከክልል 14 ምክር ቤት ቢወጡም ከ“ክልል ህወሓት” ኢታሪካዊና ጠባባዊ ክልል ያልወጡ ናቸው፡፡***

***ማ ቢወልድ ማ ማለታችንም ስለ አማራ ሕዝብ ብሶት፣ ስለዚህ ሕዝብ ማንነትና ፍላጎት፣ ማንሳት -መፃፍ አይችሉም ተብለው ከሚጠቀሱ (በህግ ሊከለከሉ ከሚገባቸው--ወያኔያው ህግን በግልባጩ ካመንበት) ግለሰቦች ውስጥ አንዱ መሆናቸውን በቅድሚያ ጠቅሰን ለማለፍ ነው፡፡***

2. *የድርሰቱ ዓላማ /የአቶ አንጻርጋቸው ተልዕኮ/ምንድነው?*

***ጓደኞችህ ማን እንደሆኑ ንገረኝና ማንነትህን እነግርሃለሁ ይላል አንድ የፈረንጆች ተረት፡፡ የአቶ አንጻርጋቸው ኢሕዴን ኢሕአዴግነት (ማለትም ሀቅ እንናገር ከተባለ ህወሓትነት) አከራካሪ አይደለም፡፡ የድርሰቱ መልዕክት የአቶ አንጻርጋቸውን ተልዕኮ ቁልጭ አድርጎ ያሳየናል፡፡ ለዚህ ከሆነ 62 ገፅ ከበቂ በላይ ነው፡፡***

***የድርሰቱ መልዕክት--የአቶ አንጻርጋቸው “ቅዱስ” ተልዕኮ--እንደሚከተለው ሊቀርብ ይችላል፣***

***ሀ / ህወሓት/ኢሕአዴግ የአማራ ህዝብ ብቸኛ ተጠሪ ብሎ የሰየመው ኢሕዴን ተልዕኮውን ማሟላት ስላልቻለ ሌላ ተለጣፊ ለማቅረብ***

***ለ / የአማራውን ሕዝብ ለመከፋፋልና ይበልጥ ለማዳከም፣***

***ሐ / ህወሓት የአማራ ትምክህተኞች የሚላቸውን ህብረ ብሄራዊ ድርጅቶች (ኢሕአፓ፣ኢዴኃቅ ወዘተ ) “አማራውን አይጠቅሙም” በሚል ከእነዚህ ኃይሎች አማራውን ለማራቅ፣ለመነጠል***

***መ / መአሕድን ለማዳከም፣***

***ሠ / ኢትዮጵያዊነትን በዚህ መንገድ ለመሸርሸር፣ ለማክሰም (ወይም ወያኔዎች እንደሚሉት “ለማምከን”)***

*ረ / የብሄርተኝነትንና የመገነጣጠልን “ የዘመኑ የፖለቲካ እውነታ” ነት ለማስረገጥ*

*በአጭሩ አቶ አንዳርጋቸው በኢትዮጵያዊነትና ኢትዮጵያ ላይ በህወሓት የተወረወሩ ፈንጂ ናቸው :: የተደበቀ ፈንጂ ተብለው ታቅደው ነበር:: ግን ፅሁፋቸው ይህንን አክሽፎታል:: አቶ አንዳርጋቸው ህወሓት/ኢሕዴን/ኢሕአዴግ ናቸው:: መልዕክታቸውም ይኸው ነው:: በአማራ ተቆርቋሪነት ካባ ኢትዮጵያዊነትን “ማምከን” :: ያው የምናውቀው የኢሕአዴግ ተልዕኮ:: 62 ገፅ በከንቱ!!*

3. <u>*ውሀ ቢወቅጡት እምቦጭ*</u>

*አቶ አንዳርጋቸው 62 ገፅ ጨርሰው በስሜታዊ ቋንቋ ሊያሳምኑን የሞከሩት ለዓመታት ወያኔና ሻዕቢያ ሲለፍፉት የነበረውን ነው:: ማለትም፤*

*ሀ / በኢትዮጵያ የብሄረሰብ ቅራኔ ዋነኛ መሆኑን፤*
*ለ / የኢትዮጵያ ኢትዮጵያነት ታሪክ የመቶ ዓመት ጉዳይ መሆኑን፤*
*ሐ / ኢትዮጵያ ኢትዮጵያዊ ማለት ሆነ በህብረብሄራዊ ድርጅት መደራጀት/መሰለፍ ኃጢያት መሆኑን::*

*የ 62 ገፅ ሑሑታ በዚህ ሊጠቃለል ይችላል:: በእርግጥ አቀራረቡ--ከቃላት አንፃር--ሊለይ ይችላል:: አቶ አንዳርጋቸው ህወሓት ተሓህት ሳለ ባወጣው ማኒፌስቶ (1968) በግልፅ እንዳስቀመጠው “ የኢትዮጵያ ብሄረሰቦች ባላቸው ቅራኔ እርስ በርስ ተጠላልተው አብረው መኖር አይቻላቸውም”:: (ስለዚህም ሁሉም ይገንጠሉ) በማለት ፈንታ “ በኢትዮጵያ ውስጥ የፖለቲካው አጀንዳ በግልፅ የብሄሮች አጀንዳ ሆኗል (ገፅ 25) ወይም “የፖለቲካ አደረጃጀቱም በብሄር ላይ የተመሰረተ ነው” (ገፅ 55) ይሉናል አቶ አንዳርጋቸው:: ቁምነገሩ ግን ያው ነው:: ህወሓት ሲለን እንደቆየው ሁሉ አቶ አንዳርጋቸውም የሚሉን ኢትዮጵያዊነት ቧልት ነው፤ የጊዜው ክስተት ብሄር መደራጀት ነው፤ “አጀንዳው የብሄሮች ስለሆነ” ህብረ ብሄር ማለት፤ኢትዮጵያ ማለት (አቶ አንዳርጋቸው በቀጥታ ባይሉትም እኛ ህወሓትን እንጥቀስና) “የሸዋ ትምክህተኞች ተንኮል ነው” የሚል ነው:: በነገራችን ላይ አቶ አንዳርጋቸው ለሸዋ አማራ ከህወሓት የወረሱት ጥላቻ በፅሁፋቸው በየቦታው አለሁ አለሁ ይላል::*

*አቶ አንዳርጋቸው ከህወሓት የሚለዩት አማራ ነኝ፤ ለአማራ ተቆርቋሪ ነኝ ብለው መቅረባቸው ብቻ ነው:: “አውላላ ሜዳ ላይ ብቻችንን ቀርተናል” (ገፅ 3) ሲሉ ኡኡ ይላሉ::እሳቸውንና መሰሎቻቸውን እያጠቃ ያለው ርቃን የመውጣት፤ አውላላ ሜዳ ላይ የመቅረት በሽታ ህዝቡን ሁሉ ነክቷል ብለው ሊያሳምኑን ይጥራሉ:: የአማራውን ስሜት “ለመኮርኮር” ተብሎ ይመስላል:: ሌሎች በብሄር ተደራጅተው ተጠናክረው አማራ ግን ተጎዳ ይሉናል:: ከተደራጁት ጋር በአንድነት ለመሄድ መጣር ደግሞ የጎታች (ህወሓት/ትግራይ ለምሳሌ) ተጎታች (አማራው) ግንኙነት ይፈጥራል (ገፅ 4) ይሉናል:: አማራው “ተዋረድኩ”--ተጎተትኩ፤ ጭራ ሆንኩ--ብሎ በንዴት በብሄር እንዲደራጅ ለመኮርኮር መሆኑ ነው:: አቶ አንዳርጋቸው ለአማራው ያለው ምርጫ በአማራነቱ መሰብሰብ መደራጀት ብቻ ነው ይላሉ (ገፅ 4 ) :: ይህ ጨቋኝ ሲባል የከረመ ሕዝብ ዛሬ በጨቋኝና ተጨቋኝ ተፈርጆ ያልመረጠው ወኪል ባልመረጠው ኃይል ተሰይሞለት ባለበት ሁኔታ እንኳ በራሱ ልደራጅ ማለቱ የሚወደድ አለመሆኑ ግልፅ ነው:: የእነ መአሕድን መከራ ያጤኗል:: ታዲያ የአቶ አንዳርጋቸው ተልዕኮ ምንድነው? ከኢሕዴንም (ድርጅታቸው) ከመአሕድም በተሻለ ለአማራው እቆምለታለሁ ሲሉ ማመን ይቻላል?*

*የአቶ አንዳርጋቸው ዋነኛ ተልዕኮ አማራውን ከኢትዮጵያዊነት፤ከሀገር ወዳድ ስሜት አርቆ በጠባብ የብሄረሰብ ብሄርተኛነት አጣብቂኝ ለመክተት ነው:: ይህ አጠቃላዩ ነው:: ሀቁ ግን--ብዙ እስት አገባ የማያሻው እውነታ ግን-- በሆነ መንገድ፤ በማንኛውም መንገድ መደራጀቱ የማይፈለግ መሆኑ ነው:: ስለዚህም ኢሕዴን የህወሓት የግል ንብረትና መሳሪያ መሆኑ የሚታወቅ በመሆኑ አቶ አንዳርጋቸው ተነጣጥረው የተተኮሱት መአሕድን ለማጥቃት፤በህብረብሄር ድርጅቶች ውስጥ ያሉ አማራዎችን ለማናጋትና በሆነ ድርጅት ያልተሰባሰቡትን አጥምደው በህወሓት/ኢሕአዴግ ዙሪያ በሽፍንፍን ለመኮልኮል ነው ማለት ይቻላል:: አማራነቱን የጠላ አማራ ብዙ እንዳይደለ ግልፅ ቢሆንም አቶ አንዳርጋቸው ግን አሌ ብለው አማራነቱን የጠላ ተበራክቷል ይሉናል (ገፅ*

19) ። አብረዋቸው በኢሕዴንና በክልል 14 ምክር ቤተ የተሰለፉትን አማራዎች ስሜት እየገለጡ
ልን መሆን አለበት። እነዚህ ደግሞ አማራነታቸውን ኢትዮጵያዊነታቸውን ባይክዱ ኖሮ ባቀፋቸ
ው ሀይል ባልታቀፉ፤ዛሬም ለሹመት ባልበቁ ነበር። አያስገርምም? ህወሓት ከኢሕአፓ ጋር
ለዓመታት ባካሄደው የቃልና የብረት ጦርነት ዋነኛው የልዩነት ነጥብ ይኸው "የብሄር ቅራኔ
አቢይነት" መሆኑ አይዘነጋም። እንደ ህወሓት አቀራረብ ብሄረሰቦች በማይታረቅ የርስ በርስ
ቅራኔ ስለሚገኙ መፍትሄውም የመገንጠል መብታቸው መረጋገጥ ስለሆነ በህብረብሄር ደረጃ
ተደራጅተው ለመላ ኢትዮጵያ እንታገል የሚሉት እነ ኢሕአፓ የአማራ ትምክህተኞችና ፀረ
ጭቁን ብሄሮች ናቸው የሚል ነበር። አቶ አንዳርጋቸው ይህንን የህወሓት አቅዋም ተቀብለው፤
መገንጠል መረጋጋጥ አለበት ብለው፤ ኤርትራ የኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት ናት ብለው፤ በ "ጨፍጫፊ
የአማራ አፄዎች" ላይ ውርጅብኝ አውርደው፤ ለኢትዮጵያ ብለው የታገሉና የተሰዉትን የልዩ
ልዩ ብሄረሰብ ተወላጆች "የአማራ ኮራኩር" ብለው አውግዘው፤ ኢሕአፓን ለኢትዮጵያ ስለታገለ
" አባይ ኢትዮጵያ " በሚል አሽሟጠው፤ ወዘተ ነው የኢሕዴን አባል የሆኑት።

አቶ አንዳርጋቸው አማራነታቸውን ቢጠሉ አይፈረድባቸውም-- አማራውም እንደጠላቸው
ማወቅ ነው የቀራቸው።

አቶ አንዳርጋቸው በኢትዮጵያዊነት ላይ የተተኮሱ ጥይት ናቸው። ለዚህም ነው ብሄርህ ተብለው
ሲጠየቁ ኢትዮጵያዊ ብለው በሚመልሱት ላይ የሚንጨረጨሩት (ገፅ 13-14)። አማራው
ከሌላው መዋለዱም ያበግናቸዋል። መቀላቀሉን አንድ ችግር ያዩታል። ወደ አማተር ሳይኮሎጂ
ም ዘው ይሉና ከሁለት ብሄረሰቦች የተወለደ ወደ አንዱ ካዘነበለ ወይ ኢትዮጵያዊነት ካለ
በታመቀ ስሜት ተሸምቆ ያልሆነ ባህርይ ያሳያል ይላሉ (ገፅ 19)። ይህ አስደናቂና ርባናቢስ
ግምገማም በአቶ አንዳ/ረጋቸው ይቀጠልበትና በርካታ ገፆችን አጥፍተው የህብረብሄር ድርጅቶች
"ፋይዳቢስነት"፤ የእነ ኢሕአፓን "ጥፋት"፤ ኢትዮጵያዊነት አማራነትን አጥፊ መሆኑን ወዘተ
እናነባለን። ድሮስ ከአቶ አንዳርጋቸው ምን ተጠብቆ?

እስቲ አንዳንድ "ፋይዳቢስ" ጥያቄዎች እንጠይቃቸው።

ሀ / የመቀላቀሉ ችግር እንዲህ አስከፉ ውጤት ካለው ምነዋ በኢሕአዴግ በባለስልጣንነት
የተሰየሙት ግለሰቦች (ታምራት ላይኔ፤ወንድወሰን/ዓይናለም ከበደ / ወዘተ ) ቀውስ ያልተነሳ?

ለ / አማራው በብሄረተኛነት በራሱ መደራጀት ካለበት ለምን ከ " ጭፍን ብሄረተኛነት" ርቆ
እንዲገኝ ከወዲሁ ተበየነበት (ገፅ 39--41)? በቀይ ሽብር የተሳተፉ፤ በሌላም ወንጀል የተሰማሩ
ኤርትራውያን በመሆናቸው በሻዕቢያ አልታቀፉም? ወያኔስ ሲመለምል ጭፍን ብሄረተኛ ትግሬ
ውን አልፈልግም አለ ወይስ በዕልልታ ተቀበለው? አማራው መከፋፈሉ ጎዳኝ፤ ከሁሉም በፊትና
በላይ አማራ ካለ፤ ሁሉን አማራ ማቀፍ እንጂ ለምን እሱ ብቻ ያማርጥ ተብሎ ይበየንበታል?

ሐ / በኢትዮጵያዊነት እንጂ በአማራነት ያልተንቀሳቀሱትን እነ መንግስቱ ንዋይን፤እነ ዋለልኝ
መኮንንን ወዘተ አቶ አንዳርጋቸው እንዴት ያደንቃሉ? ስንቱን የታሪክ ሰው-ኢትዮጵያዊ--ከእነ
ህወሓት/ሻዕቢያ ጋር ሆኖ በባሰ ደረጃ ሲያወግዝ የነበረው የኢሕዴን ዋነኛ አባል የሆኑት አቶ
አንዳርጋቸው መለስ ብለው ኢትዮጵያዊ (አማራውም) ጀግና ያጣ ይመስል የባጡ የቆጡን ሲዘረ
ዝሩ ምነዋ አልጎረበጣቸው?

መ / እነ መንግስቱ ንዋይንስ ስለ ብሄረሰብ ጥያቄ ምንም አላወሱም ነበር ብሎ መውቀሱ ምን
ይባላል? አፄ ዮሐንስስ? አፄ ልብነ ድንግልስ? እረ ስንቱስ?

በዚህ ዓይነት መቀጠል ይቻላል። ውሃ ቢወቅጡት እምቦጭ ነው። አቶ አንዳርጋቸው በ 62 ገፅ
ሌላውን ዕጥፍ ድርብ ገፆች የሚጠይቅ ውጥንቅጥን አካተው አቅርበዋል። ብልሆች ሊጓዙበት
የሚፈሩትን መንገድ ሞኞች ይሮጡበታል ይባላል። አቶ አንዳርጋቸው ውስብስብ የሆነውን
የብሄረሰብ ጥያቄ በወያኔያዊ ድፍረት ዘው ያሉበት በዚህ መልክ ነው። የብሄረ ብሄረሰብን
ምንነትና ልዩነት አልሰማሁትም ብለው ያልፉሉ።የብሄረሰብ የመገንጠል መበት የሚለው
ማርክሳዊ ሌኒናዊ መርህ በይዘቱ በርካታ ጥያቄ የተነሳበት መሆኑንም "ማን አለ?" እንኳን
ሳይሉ አልፈውታል። እነ ዋለልኝ መኮንን ስለ ብሄረሰብ ልዩነት ማንሳት ኃጢያት በሆነበት ጊዜ
(24 ዓመት በፊት) በስሜትና በተወሰነ ርዕዩተዓለም ተፅዕኖ የፃፉትን ገልብጠው እነሆ በማለት

ይወሰናሉ:: ዋለልኝ ተሳስቷል የማንላቸው መስሏቸው ሊሆን ይችላል::

እስቲ የአቶ አንዳርጋቸውን ወያኔያዊ የሞኝ ግልቢያ ሁለት ነጥቦችን በማንሳት እናሳይ::

ሀ / "ብሄረሰቦች አሉ ካልን" ይላሉ አቶ አንዳርጋቸው (ገፅ 7 ) " የእነዚህ ብሄር/ ህዘቦች የማንነት መግለጫ ብሄረተኛነት ከመሆን ሊያመልጥ አይችልም" በሚል በድፍረት ያስረግጣሉ::

ግሩም! አቶ አንዳርጋቸው የሚሉን "ኢትዮጵያዊ" የሚባል ፍጡር (ማንነት) የለም ነው:: መልካም:: በዚህ ዓይነት አንድ ቋንቋ የማይናገር "አንድ" ያልሆነ ህዝቦችን ያካተተ ሀገር ሀገሬ የሚላት አይኖርም ማለት ነው:: በአሜሪካ ያሉ ቋንቋቸውን ያልተዉ ጣሊያኖች፣ፖሊሾች፣ ጀርመኖች፣ ፈረንሳዮች፣ስፓንያርዶች፣ ወዘተ አሜሪካዊ ነን አይሉም ማለት ነው:: መለያቸው አሜሪካዊነት አይደለም ማለት ነው:: ሌላም ሌላም መጥቀስ ይቻላል:: አቶ አንዳርጋቸው የጉዳዩን ግልባጭ ማንሳቱን ስላልመረጡ እኛ እናንሳው:: አንድ ቋንቋ የሚናገሩ ፣በሀይማኖት በባህል አንድ የሆኑ ሶማሌዎች ምነዋ ተከፋፍለው ተነካከሱ? አቶ አንዳርጋቸው ልዩ ልዩ ብሄረሰቦች ባሉባት ሀገር የህዝብ ማንነት መግለጫ የብሄረሰቡ ብሄርተኝነት ነው ያሉት ከጠባብነት ባሻገር የድንቁርና ምልክት ነው:: ይህም ስድብ ሳይሆን ለዘብተኛ ግምጋሜ ነው::

ለ / "ብሄርተኝነት በጉትጎታና በቅስቅሳ የመጣ አይደለም ይላሉ " አቶ አንዳርጋቸው (ገፅ 12)

ተባለ!! ለብሄርተኝነትና በዚህም ለሚመሰረት ትግል ተጨባጭ ምክንያቶች ሊኖሩ እንደሚችሉት ሁሉ ብሄርተኝነት በጉትጎታና በቅስቅሳ ሊመጣ ይችላል:: በኤርትራም በትግራይም ታይቷል:: ልገንጠል የማይለውን ሕዝብ ካለተገነጠልክ ብለው ለከረረ አቅዋም ቀን ተሌት የሚገፋፉት ታይተዋል:: በሰላም አብሮ ሲኖር የነበረውን ሕዝብ ቆስቁሰው ከፋፍለውና ለኳኩሰው ርስበርሱ እንደሚያፋጁትም ታይቷል ለማለት አርባጉት ማለት አንገደድም:: ብሄርተኛ ድርጅቶችን በአብዛኛው የሚያንቀሳቀሱት ክፍሎች የጉትጎታና የቅስቀሳ ችሎታቸው አንሶ አልተገኘም:: ይህንንም ከሁሉም በላይ አቶ አንዳርጋቸው እንደሚያውቁ ግልፅ ነው::

አቶ አንዳርጋቸው ዛሬ ናቅፋ የለም ብለዋል (ገፅ 53) :: እውነት:: ዕድሜ ለድርጅታቸው ለኢሕአዴግ ኤርትራ ራሷስ የት አለችና? አቶ አንዳርጋቸው በፅሁፋቸው ከፈፀሙት አፀያፊ በደል አንዱ ለኢትዮጵያ ብለው ህይወታቸውን የሰጡትን ጀግኖች "የአማራ ታጋዮች" በሚል በብሄርተኛ ጥላሸታቸው መቀባታቸው ነው:: እነ ዋለልኝ ሆኑ ለኢትዮጵያ ብለው የተሰዉት የኢሕአፓ አባላት በጠባብነት (አማራ ተባለ ሌላ) መነሳታቸው አሳዛኝ ነው:: ከአቶ አንዳርጋቸው ሌላ ምን ይጠበቃል ብሎ ማለፉ አይበቃም:: " የአማራ ውድ ልጆች የወደቁለት የዴሞክራሲና የሕዝቦች እኩልነት መብቶች....መከበር በመንግስት ደረጃ ህግ እንዲሆን አስችሏል" ም ብለዋል አቶ አንዳርጋቸው (ገፅ 51/ስርዝ የእኔ) :: ውሻ በበላበት ይጮኻልና የሾማቸውንና እያሸሞነሞናቸው ያለውን ሀይል ማወደሳቸው የሚጠበቅ ቢሆንም " የኢትዮጵያ ውድ ልጆች" ለማንና ለምን እንደ ተሰዉና አሁንም እየተሰዉ እንዳሉ ህዝባችን ጠንቅቆ ያውቀዋል:: የወቅቱ የፖለቲካ አጀንዳ የብሄሮች አጀንዳ ሆኗል ብለዋል አቶ አንዳርጋቸው:: በኢሕአዴግ አጀንዳ አርቃቂነት ከሆነ ትክክል ነው:: የሕዝባችን አጀንዳ ከሆነ ሌላ ነው:: ገዢዎች "አጀንዳ" የሚሉት የእሱ እንዳልሆነ ና ከስርዓታቸውም ጋር ተኖ እንደሚጠፋ ጠንቅቅ ያውቀዋል:: ለመንግስቱ ኃይለ ማርያም የወቅቱ የወቅቱ የፖለቲካ አጀንዳ ምን እንደነበር እናውቃለን::

የኢትዮጵያ ህዝብ ራሱን በቻለ የታሪክ ሂደትና ውጣ ውረድ የጋራ ታሪክ የጋራ ባለቤት ሆነዋል:: ልዩ ልዩ ብሄረሰቦች ኖራቸው ኢትዮጵያዊነትን የሚሰርዝ ሳይሆን ይህንኑ ሀገራዊ ስሜት የሚያጠናክር መሆኑን አሳይተዋል:: በእኩልነት ላይ የተመሰረተ አንድነትን ለማጠናከር ከመጣር ቦዝነው አያውቁም:: ዛሬም እንደትላንቱ ይህ የዴሞክራሲያዊ ትግላቸው እምብርት ነው:: አቶ አንዳርጋቸው በቅጡ የማያውቁት ትግል ሊሆን ይችላል:: ግን ከተማሪው እንቅስቃሴ፣ ከገበሬው አመፅ፣ ከየካቲት 66 አስካሁን በህዝብ በአጀንዳነት ያለው ብሄርተኝነትን ማስፈን ሳይሆን ኢትዮጵያዊነት በእኩል የሁሉንም ማንነት ገላጭ ሆኖ ዴሞክራሲ እንዲሰፍን ነው:: ኢትዮጵያን ለማፍረስ ለመገነጣጠል ሳይሆን:: አቶ አንዳርጋቸው " ውድ የአማራ

ልጆች” የሚሏቸው ግን በሀቁ “ውድ የኢትዮጵያ ልጆች” የሆኑ ሁሉ ፤ አማራ፤ኦሮሞ፤ጉራጌ፤ትግሬ፤ ሲዳማ፤አገው፤ ወዘተ ሳይሉ--ሳይለያዩ፤ በብሄርተኝነት “ማንነት” ሳይፈራቀቁ--የተዋደቁትና አሁንም እየታገሉ ያሉት ለዚህ ነው፡፡ በጠባቦች ጎራ ይህ እውነታ ሰቅጣጭ “ የትምክህተኞች ልፈፋ” ተብሎ ቢወሰድ አያስገርመንም፡፡ አቶ አንዳርጋቸውም ጎራቸው ዛሬም ከእነዚህ ዓይነቶቹ በመሆኑ እንደ አለቆቻቸው አሳፋሪ መፅሀፍ ( የኤርትራ ሕዝብ ትግል ከየት ወዴት? ህወሓት 1979) የበኩላቸውን ከየት ወዴት ድርሰት ጫጭረው ኳተነው ፈቅ ለማለት ቢያቅታቸው አያስገርም ይሆናል፡፡ ሊዊስ ካሮል በፃፈው “አሊስ ኢን ወንደርላንድ” መፅሀፍ ውስጥ አንዱ ሲናገር “ባለንብት ለመቆም ብዙ መሮጥ ይኖርብናል” ያለውን ያስታውሰናል፡፡ የረግረግ ሩጫ፡፡

ይቺ የመቶ ዓመት ታሪክ ብቻ አላት የምትባል  ውድ ሀገራችን የሶስት መቶ ዓመት እንኳን ታሪክ በሌለው ኃያል መንግስት በተሾሙ ባለነፍጦች የምትጠፋ አለመሆኗ ጥርጥር የለውም፡፡ የአቶ አንዳርጋቸው የህወሓትን ልፈፋ ደጋሚ ድርሰት በርግጥም ፋይዳ ቢስ ነው፡፡ ጊዜ ሲያመች የምንጠይቃቸው ብዙ ነገር ስላለ  ለድርሰቷ መግዣ ያወጣነውን ሶስት ብር አንጠይቅም፡፡ ገቢያቸውን “ አለረዳት ለቀረው ለአማራው ሕዝብ” ያውሉት እንደሆነ ግን እናያለን፡፡ የመታዘብ ችሎታም በብሄርተኝነት ላልተሰለፉ አይፈቀድም እስካልተባለ ድረስ፡፡

በመጨረሻም ለአቶ አንዳርጋቸው አንድ መልዕክት አለኝ፡፡ የአማራው ሕዝብ፤ ያ ህወሓት “ከአማራው ገዢ መደብ ተረፍ መረፍ (ፍርፋሪ) በማግኘት ጨቋኝ ብሄር ሆኗል/ነው” ተብሎ የተወገዘው ህዝብ፤ ከሁሉም ኢትዮጵያዊ ሀገር ወዳድ ህዝብ ጎን ቆሞ ለኢትዮጵያ ይታገላል እንጂ በኋላቀር ጠባብ ብሄርተኛ ማጥ ገብቶ የሚጨማለቅ አለመሆኑን ማወቅ ያስፈልጋል፡፡

ነሐሴ 1985